**የኢትዮጵያ ጉምሩክ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 1080/2017**

**Ethiopia Customs Valuation Directive Number 1080/2025**

የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ከዓለም ንግድ ድርጅት የጉምሩክ የዋጋ አተማመን ስምምነት መርሆዎች እና ዘዴዎች ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ፤

WHEREAS, the Ethiopian Customs Valuation System needs to be aligned with the World Trade Organization's Customs Valuation Agreement principles and methods,

ኢትዮጵያ ተቀብላ ካጸደቀቻቸው ዓለማቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጣናዊ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ሥርዓት ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, Ethiopia is required to design and implement a customs valuation system that complies with international, continental, and regional agreements it has accepted and ratified,

የጉምሩክ ዋጋ አተማመን በጉምሩክ አዋጅ የተደነገጉ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች መፈጸም የሚያስችል ግልጽ መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is necessary to establish clear guidelines to ensure the implementation of customs valuation principles and regulations as stipulated in the Customs Proclamation,

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 180 /2/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

Now, therefore, the Ministry of Revenues, pursuant to the authority granted under Article 180(2) of the Customs Proclamation No. 859/06 (as amended), has issued this directive.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 1080/2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ገቢ ዕቃ"** ማለት ወደ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የሚገባ ማንኛውም ዕቃ ሲሆን ገንዘብን አይጨምርም።

2) **"ወጪ ዕቃ"** ማለት ከኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የሚወጣ ማንኛውም ዕቃ ሲሆን ገንዘብን አይጨምርም።

3) **"የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ"** ማለት በጉምሩክ አዋጅ እና በዚህ መመሪያ በተደነገጉት የዋጋ አተማመን ዘዴዎች አማካኝነት የሚሰላ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባው የሲ.አይ. ኤፍ ዋጋና ሌሎች ወጪዎችና ክፍያዎች ጠቅላላ ድምር ነው።

4) **"የማነፃፀሪያ ዋጋ"** ማለት በዕቃ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበውን የዕቃ ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራት እና ለመወሰን የሚያገለግል በጉምሩክ ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ ዋጋ መረጃ ነው።

## Part one
## General Provisions

### 1. Short Title

This Directive may be cited as the Ethiopian Customs Valuation Directive Number1080/2025.

### 2. Definitions

Unless the context of the term provides a different meaning, the following definitions apply in this directive:

1) **"Imported Goods"** means any goods entering the Ethiopian Customs Territory, excluding currency.

2). **"Exported Goods"** means any goods leaving the Ethiopian Customs Territory, excluding currency.

3). **"Customs Duty and Tax Payable Value**" means the total value calculated using valuation methods specified in the Customs Proclamation and this guideline, comprising the CIF price paid or payable for the goods up to the first entry point into the Ethiopian Customs Territory, plus other costs and charges.

4. "**Reference price**" means accepted customs price data used to verify and determine the accuracy of the declared value of goods provided by the declarant.

5) **“የመነሻ ዋጋ “**ማለት አስመጪው ስለሚያስመጣው ዕቃ ትክክለኛና እውነተኛ የዕቃ ዋጋ ከትክክለኛ የግዥ ሰነዱ ጋር ለኮሚሽኑ ማቅረብ ባልቻለ ዕቃ ላይ የኮሚሽኑ የዋጋ ትመና ዳይሬክቶሬት ከትክክለኛ የዋጋ መረጃ ምንጭ የሚያደራጀው የዕቃ ዋጋ ማለት ነው፡፡

**5. "Base Price"** means the price of goods organized by the Commission’s Valuation Directorate from reliable price data sources when an importer fails to provide accurate and authentic price information with valid purchase documents.

6) **"የኤፍ.ኦ. ቢ ዋጋ** /FOB Price/” ማለት የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና በላኪ አገር እስከ የመጨረሻ መጫኛ ቦታ /ወደብ/ ድረስ ለዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ወጪ ድምር ነው፡፡

6. "**FOB Price**" means the sale price of goods plus costs paid or payable in the exporting country up to the final loading point/port.

7) **"የሲ.አይ. ኤፍ ዋጋ** /CIF Price/” ማለት የዕቃው የመሸጫ ዋጋ እና በላኪ አገር እስከ የመጨረሻ መጫኛ ቦታ /ወደብ/ ድረስ ለዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ወጪ እና ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የኢንሹራንስ፣ የማጓጓዣ፣ የማስጫኛ፣ የማውረጃ እና የመንከባከቢያ ወጪ ድምር ነው፡፡

**7. "CIF Price"** means the sale price of goods, costs paid or payable in the exporting country up to the final loading point/port, plus insurance, transport, loading, unloading, and handling costs to deliver the goods to Ethiopia’s first entry point.

8) **"የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት** (Ethiopian Customs Valuation System /ECVS-G2)” ማለት በኮሚሽኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ወይም ወጪ ዕቃ ዋጋ መረጃን እና የዓለማቀፍ ዕቃ ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደራጅ ለዋጋ ማነጻጸሪያነት የሚያገለግል የመረጃ ሥርዓት ነው፡፡

**8. "Ethiopian Customs Valuation System (ECVS-G2)"** means a data system used for price comparison, based on accepted import/export price data and international price information, managed by the Commission.

9) **"በአንድ አገር የተመረተ ዕቃ”** ማለት በአንድ ሉኣላዊ ሀገር የተመረተ ዕቃ ማለት ሲሆን በተፈጥሮ ወይም በቁፋሮ የተገኘ ዕቃን ይጨምራል፡፡

**9. "Goods Produced in One Country"** means Goods produced in a single sovereign country, including those obtained naturally or through extraction.

10) **"በተመሣሣይ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገሮች"** ማለት በዓለም የንግድ ድርጅት ወይም በተባበሩት መንግስታት የአገሮች የእድገት ደረጃ ዝርዝር መሰረት በተመሳሳይ ዕድገት ደረጃ የሚገኙ አገራት ሲሆኑ የአህጉራዊ ነባራዊ ሁኔታንም ከግንዛቤ የሚያስገባ የአገራት ዝርዝርን ይጨምራል።

**10. "Countries at Similar Development Levels"** means countries at similar stage of development as per the World Trade Organization or United Nations lists, including continental situational considerations.

11) **"ተቀራራቢ ዕቃ"** ማለት በአንድ አይነት ኢንዱስትሪ ወይም በአንድ አይነት የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመረት ዕቃ ሲሆን የአንድ ዓይነት ዕቃና ተመሳሳይ ዕቃን ይጨምራል።

**11. "Comparable Goods"** means goods produced in the same industry or sector, including identical and similar goods.

12) **"የአገር ውስጥ ገበያ ነጠላ መሸጫ ዋጋ"** ማለት ወደ አገር ውስጥ የገባው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ አገር ውስጥ የገባና በገባበት ሁኔታ በከፍተኛ ብዛት የተሸጠበት ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስን አይጨምርም።

**12. "Domestic Market Single Sale Price"** means the price at which identical or similar imported goods are sold in significant quantities in the domestic market at the same or comparable time, excluding value-added tax.

13) **"የጉምሩክ ዋጋ ማጣራት"** ማለት በሚመለከተው የጉምሩክ ባለሙያ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የተገለጸው የዕቃ ዋጋ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ወይም ለማጣራት መነሻ የሆኑ ሰነዶችን የመመርመር ሂደት ነው።

**13. "Customs Valuation"** means the process of examining documents by the relevant customs officer to verify or ascertain the accuracy of the declared value of goods.

14) **"የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ** /Valuation Details Declaration (VDD)/" ማለት ከዕቃ ዲክላራሲዮን በተጨማሪ የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችና መረጃዎችን በዲክላራሲዮን አቅራቢው በዝርዝር ተሞልቶ ለኮሚሽኑ የሚቀርብበት የኤሌክሮኒክስ መረጃ ማሳወቂያ ሥርዓት ነው።

**14. "Valuation Details Declaration (VDD)"** means an electronic notification system where the declarant provides detailed statements and information, in addition to the goods declaration, to determine the customs duty and tax payable value of imported goods.

15) **"የንግድ ደረጃ"** ማለት ሻጭ ድርጅቶች ባላቸው የንግድ ሽያጭ ሰንሰለት ቅደም ተከተል መሰረት የአንድ ዕቃ ዋጋ በአምራች፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ደረጃ ሊለያይ የሚችልበትን የንግድ ሁኔታ የሚያሳይ ደረጃ ነው።

**15. "Commercial Level"** means the stage in the commercial sales chain (e.g., manufacturer, distributor, or retailer) that may affect the price of goods.

16) **"ሚኒስቴር እና ሚኒስትር"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር እና ሚንስትር ነው።

**16. "Ministry and Minister"** means the Ministry of Revenues and its Minister.

17) **"ኮሚሽን እና ኮሚሽነር "**ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን እና ኮሚሽነር ማለት ሲሆን ኮሚሽን የሚለው ሁሉንም የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የሚጨምር ነው።

**17.** "**Commission and Commissioner**" means the Customs Commission and its Commissioner, with Commission including all customs branch offices.

18) **"ዳይሬክቶሬት"** ማለት የጉምሩክ ዋጋ ትመና ዳይሬክቶሬት ነው።

**18.** "**Directorate**" means the Customs Valuation Directorate.

19) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት የተሰጠው ነው።

**19.** "**Person**" means a natural person or a legal entity.

20) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና የተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 ነው።

**20.** "**Proclamation**" means Customs Proclamation No. 859/2006 and its amendment, Customs Proclamation No. 1160/2011.

21) **"ደንብ"** ማለት የጉምሩክ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 437/2011 እና የጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014 ነው።

**21.** "**Regulation**" means Customs Establishment Regulation No. 437/2011 and Customs Regulation No. 518/2014.

22) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላት እና ሐረጎች በአዋጁ እና ደንቦቹ ላይ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

**22.** Other Terms and Phrases not defined in this directive shall carry the meanings assigned in the Proclamation and Regulations.

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

## 3. Scope of Application

ይህ መመሪያ፡-

1. ወደ ሀገር በሚገባ እና በሚወጣ ማንኛውም ዕቃ፣

2. ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ከጉምሩክ ቁጥጥር የተለቀቀ ዕቃ ወይም የተሟላ የጉምሩክ ስነስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ሆኖ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

3. የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ተፈጽሞበት በተለቀቀ ዕቃ ላይ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሲከናወን፣

4. ንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደ ሀገር በሚገባ ወይም/እና በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የሚገባ ዕቃ ዋጋ አተማመን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

This directive applies to:

1. Any goods entering or leaving the country,

2. Goods released from customs control without payment of duties and taxes, or goods for which the full customs procedure has not been completed, when it is deemed necessary to pay duties and taxes,

3. Goods released after customs procedures, subject to a post-clearance audit,

4. Goods imported for non-commercial purposes or temporarily imported, with regard to their valuation.

## ክፍል ሁለት
## ስለጉምሩክ ዋጋ አወሳሰን ሁኔታ
### ምዕራፍ አንድ
### የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ዘዴ

## Part Two
## On the Conditions of Customs Valuation
### Chapter One
### Methods of Customs Valuation

4. **መርህ**

1) የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚከተሉት መርሆዎች መሰረት በቅደም ተከተል በመጠቀም ይሆናል።

ሀ) የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴን፣

ለ) የአንድ አይነት ዕቃ የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴን፣

ሐ) የተመሣሣይ ዕቃ የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴን፣

መ) ወደ ኋላ የማስላት ዋጋ አተማመን ዘዴን፣

ሠ) በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ ዋጋ አተማመን ዘዴን እና

**4. Principles**

1. The determination of customs duty and tax value shall be based on the following principles in the order of priority:

a) Transaction Value Method,

b) Transaction Value of Identical Goods Method,

c) Transaction Value of Similar Goods Method,

d) Deductive value method,

e) Computed value method, and

ረ) ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ

f) Fallback value method.

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ በአስመጪው ጥያቄ በፊደል ተራ (መ) እና (ሠ) ቅደም ተከተል ተቀያይሮ ሊተገበር ይችላል።

2. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this article, at the request of the importer, the order of application of paragraphs (d) and (e) may be reversed.

## 5. የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ

## 5. Transaction Value Method

1) ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ተደርጐ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠ ዕቃ በትክክል የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባ የግብይት ዋጋ ወይም የተከፈለበት የተረጋገጠ የአምራች የዕቃ ዋጋ ሲሆን በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች ታክለውበት በዲክለራሲዮን አቅራቢው ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ የዕቃዎች ትክክለኛ ማስረጃ በኮሚሽኑ የዕቃዎች የዋጋ መተመኛ ሰነድ ተደርገው የሚወሰዱና በዚሁ አግባብ ተፈፃሚ የሚደረጉ ናቸው።

1. The transaction value for goods imported into Ethiopia is determined based on the price actually paid or payable for goods sold for export to Ethiopia, including additional charges specified in the proclamation and this guideline. The declarant must provide accurate evidence of the goods' value to the Customs Commission, which is assessed using the Commission's valuation documents and applied accordingly.

2) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የዕቃ ዋጋ እና ሰነድ በቀጥታ ተቀባይነት የማይኖረው ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 90 /1//ሀ/-/መ/ የተቀመጡት መስፈርቶች ካልተሟሉ ኮሚሽነሩ ወይም በየደረጃው ለዚሁ አፈፃፀመም ሲባል ተግባርና ኃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ስራ ኃላፊ፣ ፣ የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ባለሙያ፣ የጉምሩክ ዋጋ ትመና ባለሙያ ፡-

2) If the declared value or documents provided by the declarant are not acceptable or raise doubts, and the requirements under Article 90(1)(a)-(e) of the proclamation are not met, the Customs Commissioner, responsible customs officer, document examiner, or valuation expert may act if:

ሀ/ በዋጋ ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የዕቃው መግለጫዎች፣ የብዛት፣ የዓይነት፣ የጥራት፣ የመለኪያ፣ የምርት ሀገር፣ የምርት ዘመን መግለጫዎች እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ማስረጃዎች በትክክል አለመገለጻቸውን ወይም አለመቅረባቸውን ያረጋገጠ ከሆነ ወይም፣

a) Descriptions of the goods (quantity, type, quality, measurements, country of origin, production date) or other essential information/evidence are not accurately provided or are missing,

ለ/ በሀሰት ወይም በተጭበረበረ መልኩ የተዘጋጀ ሰነድ/ሀሰተኛ ማስረጃ የቀረበ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ማስረጃ ካለው ወይም፣

b) There is confirmed evidence of falsified or fraudulent documents,

ሐ/ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 96 ላይ የተጠቀሱት ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ ካልተካተቱ ወይም ዋጋቸውን ለመተመን የሚያስችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎች ዲክላራሲዮን አቅራቢው አለማቅረቡን ካረጋገጠ፤

c) Additional charges specified in Article 96 of Customs Proclamation No. 859/2006 are not included in the transaction value or lack verifiable evidence,

መ/ በዲክለራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የግብይት ዋጋ ግልጽ በሆነ መስፈርት እና በገበያ ትንታኔ የእቃው ዋጋ ላይ ተመስርቶ ሲታይ ኮሚሽኑ በቀረበለት የግብይት ዋጋ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ያደረበት ከሆነ ወይም ዲክልልራሲዮን አቅራቢው ተጨማሪ ሕጋዊ ማስረጃዎችን አቅርቦ እንዲያስረዳ ተጠይቆ ይህንኑ ሕጋዊ ማስረጃን በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ፥

d) If the Commission has doubts about the accuracy of the transaction value presented by the declarant, based on transparent criteria and market analysis, or if the declarant is requested to provide additional legal evidence to substantiate the declaration and fails to submit such legal evidence within 15 days,

ሠ/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (መ) አፈፃፀም ሲባል ‹‹ተጨማሪ ህጋዊ ማስረጃ›› ማለት ዕቃው የተገዛበትን የግዢ/ሽያጭ ውል፣ በባንክ የተረጋገጠ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣ ከአምራች ድርጅቱ ተረጋግጦ ወደ ኮሚሽኑ በቀጥታ የሚመጣ የአምራች ዕቃ ዋጋ ማስረጃ ወይም የዲክላራሲዮን አቅራቢው ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ማስረጃ እና ሌሎች ከዕቃው ግዥ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎች ናቸው።

e) For sub-article (d), “additional legal evidence” includes purchase/sale contracts, bank-verified proforma invoices, manufacturer’s price evidence sent directly to the Commission, or other documents related to the goods’ purchase.

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲከሰቱ የሚከተሉት ተግባራት በቅደም ተከተል ይፈፀማሉ፡-

3) When the conditions listed in sub-article 2 of this article occur, the following actions shall be carried out in sequence:

ሀ/ የጉምሩክ ስራ ኃላፊው፣ የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ባለሙያው እና የጉምሩክ ዋጋ ትመና ባለሙያው የዲክላራሲዮን አቅራቢውን ዋጋ የጠረጠሩበትን በቂ ህጋዊ ምክንያቱን ምክንያት በመግለጽ ዲክላራሲዮን አቅራቢው

a) The customs officer, the customs document examiner, and the customs valuation expert shall, with sufficient legal justification, request the declarant to either

በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም ስለ ዕቃው ዋጋ ትክክለኛነት የሚያስረዱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ እንዲያቀርቡ ይጠይቃሉ፣

appear in person to provide an explanation or submit additional evidence proving the accuracy of the declared value of the goods within 15 consecutive days.

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/መ/ የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የዕቃው የግብይት ዋጋ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የዕቃው ዋጋ በአለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የዋጋ ለውጥ መኖሩን ወይም/እና በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የዕቃው የግብይት ዋጋ ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆኑ ተጣርቶ ከተረጋገጠ ወይም ዲክለራሲዮን አቅራቢው ያቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክለኛ የአምራች ዕቃ ዋጋ ስለመሆኑ በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ለኮሚሽነሩ ወይም በየደረጃው ለዚሁ አፈፃፀም ሲባል ተግባርና ኃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ስራ ኃላፊው ወይም የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ባለሙያው ወይም የጉምሩክ ዋጋ ትመና ባለሙያው በዚሁ አግባብ በዲክለራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ትክክለኛ የዕቃው ዋጋ ማስረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ ያስተናግዳል።

b) When the situation specified in sub-article 2(b) arises, the transaction value of the goods submitted by the declarant may be accepted if: the declared value is consistent with internationally recognized price changes, or the transaction value provided by the declarant is verified as accurate, or the declared value is substantiated as the correct manufacturer's price with tangible evidence. The Commissioner, or the customs officer, customs document examiner, or customs valuation expert assigned responsibility at the respective level, shall process the declaration by accepting the accurate value of the goods provided by the declarant.

ሐ/ ዲክለራሲዮን አቅራቢው የተጠየቀውን የዕቃው ትክክለኛ የግብይት ማስረጃ ወይም የተረጋገጠ ትክክለኛ የአምራች የዕቃ ዋጋ ማስረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት በኮሚሽኑ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረበ ኮሚሽነሩ ወይም በየደረጃው ለዚሁ አፈፃፀም ሲባል ተግባርና ኃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ስራ ኃላፊ ወይም የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ባለሙያ ወይም የጉምሩክ ዋጋ ትመና ባለሙያ ህጋዊ ውሳኔያቸውን በማሳወቅ በሚቀጥለው የዋጋ አተማመን ዘዴ የዕቃውን ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ወስነው መክፈል የሚገባውን ህጋዊ ቀረጥና ታክስ ያስከፍላሉ።

c) If the declarant fails to provide the requested evidence of the accurate transaction value or verified manufacturer's price within the time limit set by the Commission as per sub-articles (a) and (b), the Commissioner, or the customs officer, customs document examiner, or customs valuation expert assigned responsibility at the respective level, shall notify their legal decision and determine the customs duty and tax payable based on the next applicable

valuation method, ensuring the legally required duties and taxes are imposed.

## 6. የገዥና ሻጭ መካከል ግንኙነት አለ ተብሎ በሚጠረጠርበት ጊዜ ስለሚኖር አሰራር

## 6. The procedure to be followed when a relationship is presumed to exist between the buyer and the seller

1) የቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከሻጭ ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑንና ግንኙነቱ በግብይት ዋጋው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ስለመሆኑ በበቂ ምክንያት ከጠረጠረ በልዩነት ለሚፈለገው የቀረጥና ታክስ መጠን በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ በማድረግ ቀጣይ ማጣራት እንዲደረግ ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት ያሳውቃል።

1. If the customs expert or work supervisor of the Customs Office has sufficient reason to suspect that the declarant has a relationship with the seller and that this relationship affects the transaction value, they shall require the provision of adequate security for the amount of duty and tax required due to the difference and notify the Price Assessment and Development Directorate to conduct further investigation.

2) ዳይሬክቶሬቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት የቀረበለትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

2. Based on the request submitted under sub-article (1) of this article, the Directorate shall conduct the necessary investigation and make a decision on the matter.

## 7. በሻጭና በገዥ መካከል ግንኙነት ስለመኖሩ የሚደረግ ማጣራት

## 7. Verification of the Existence of Relationship Between Seller and Buyer

1) በሻጭና በገዢ መካከል ግንኙነት ሲኖር ግንኙነቱ በቀረበው የዕቃ ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ስለማሳደሩ ለማረጋገጥ፡-

**1)** To confirm whether the relationship between the seller and the buyer affects the price of the goods offered:

ሀ/ የዕቃው ዋጋ የተወሰነበት ሁኔታ በተለይ ዕቃውን በሚያመርተው የኢንዱስትሪ ዘርፍ በማንኛውም ነፃ የገበያ ውድድር ውስጥ ትክክለኛ ዋጋ በሚወሰንበት ሁኔታ የተወሰነ መሆኑን፣

a) The price of the goods must be determined under conditions where, in the relevant industry producing the goods, the price is set in a free and competitive market environment.

ለ/ የዕቃው ዋጋ የተወሰነው ከሻጩ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች በተወሰነበት ሁኔታ መሆኑን፣

b) The price of the goods must be determined under conditions applicable to buyers who have no relationship with the seller.

ሐ/ የግብይት ዋጋው አጠቃላይ ዕቃውን ለማምረት የሚጠይቀውን ወጪ እና አምራቹ በተመሳሳይ ወቅት ተመሳሳይ ዕቃ በመሸጥ ከሚያገኘው ትርፍ ጋር የሚመጣጠን ትርፍ ሊያስገኝ የሚችል መሆኑን ማጣራት አለበት።

c) It must be verified that the transaction price covers the overall cost of producing the goods and allows for a profit comparable to what the producer would earn from selling similar goods at the same time.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት ግንኙነት ባላቸው አካላት መካከል በተደረገ ግብይት የቀረበው የዕቃው ዋጋ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ተቀባይነት ይኖረዋል።

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the price of goods offered in a transaction between related parties, as stipulated in Article 90 of the Proclamation, will be accepted if one of the following conditions is fulfilled:

ሀ/ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አለመኖራቸውን ሲረጋገጥ ወይም

a) It is confirmed that the conditions listed in Article 5, Sub-Article 2 are not present; or

ለ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጠ የአንድ ዓይነት ወይም የመሳሳይ ዕቃ የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በማነፃፀሪያ የዋጋ መረጃ ውስጥ ከሚገኝ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በልጦ የተገኘ እንደሆነ ወይም በአንቀጽ 5(3)/ለ/ መሰረት ተቀባይነት ካገኘ፤

b) When compared with the transaction price of identical or similar goods sold to unrelated buyers at the same time, it is found to be higher than or equivalent to the price of identical or similar goods in comparative price data, or it is accepted under Article 5(3)(b); or

ሐ/ ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ከተወሰነ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማነፃፀሪያ የዋጋ መረጃ ውስጥ ከሚገኝ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም በአንቀጽ 5(3)/ለ/ መሰረት ተቀባይነት ካገኘ፤ ወይም

c) When determined using the deductive calculation method, the price of identical or similar goods is found to be equivalent or comparable to the price of identical or similar goods in comparative price data, or it is accepted under Article 5(3)(b); or

መ/ በወጪ ስሌት ላይ የተመሰረተ የማስላት ዘዴ ከተወሰነ አንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች በማነፃፀሪያ የዋጋ መረጃ ውስጥ

d) When determined using the cost-based calculation method, the price of identical or

ከሚገኝ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም በአንቀጽ 5(3)/ለ/ መሰረት ተቀባይነት ካገኘ፤

similar goods is found to be equivalent or comparable to the price of identical or similar goods in comparative price data, or it is accepted under Article 5(3)(b).

3) ዳይሬክቶሬቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ያደረገው የማጣራት ሂደት ውጤት በተመለከተ ለቅ/ጽ/ቤቱና ለዲክላራሲዮን አቅራቢው ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ከማሳወቁ በተጨማሪ በማነፃፀሪያ የዋጋ መረጃ ውስጥ መረጃውን እንዲመዘገብ ያደርጋል፡፡

3) The Directorate shall, within 15 days from the date the relationship is confirmed, notify the Customs Office and the declaration provider in writing of the results of the verification process conducted under this Article. Additionally, it shall ensure that the information is recorded in the comparative price data system.

4) ቅ/ጽ/ቤቱ ግንኙነት ያላቸው አካላት አስመልክቶ የተሰጠውን የዋጋ ውሳኔ እና በዋጋ መረጃ ሥርዓት የተመዘገበውን መረጃ መነሻ በማድረግ ዲክላራሲዮን አቅራቢው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በቀጣይ ከሻጩ ሲያስመጣ ሌላ የተለየ ሁኔታ ወይም መረጃ እስካልተነኘ ድረስ በዚሁ መሠረት ተመሳሳይ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) Based on the pricing decision regarding related parties and the information recorded in the price data system, the Customs Office may make the same decision for identical or similar goods imported by the declaration provider from the same seller in the future, unless a different condition or information arises.

## 8. የአንድ አይነት ዕቃ የግብይት ዋጋ አወሳሰን ዘዴ

## 8. Method for Determining the Transaction Value of Identical Goods

1) የዕቃውን ዋጋ በግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ መወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 91 በተደነገገው መሠረት ዕቃው ከመግባቱ በፊት በነበሩት 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩና ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጡ የአንድ አይነት ዕቃዎች አስመልክቶ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

1) If the transaction value of goods cannot be determined using the standard method, as per Article 91 of the regulation, the value is determined based on the price information provided by the declarant for identical goods sold to unrelated buyers at the same commercial level and in comparable quantities, imported into the country within the 90 days prior to the goods' entry.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 91 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት፡-

2) If the transaction value cannot be determined under sub-article (1), as per Article 91, sub-article (2):

ሀ/ ተመሣሣይ ንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ፣

**a)** For goods at the same commercial level but not sold in comparable quantities,

ለ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ወይም

**b)** For goods at a different commercial level but sold in comparable quantities, or

ሐ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ያላቸውና በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ አንድ አይነት ዕቃዎችን የንግድ ደረጃው ወይም የብዛት ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ አይነት ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ አድርጐ መጠቀም ይቻላል።

**c)** For goods at a different commercial level and not sold in comparable quantities, the transaction value of identical goods imported into the country can be used after adjusting for differences in commercial level or quantity.

መ/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ደረጃ እና ተቀራራቢ ብዛት ለሚያስከትለው ልዩነት ማስተካከያ የሚደረገው በዲክለራሲዮን አቅራቢው የሚቀርበው ማስረጃ በሻጩ የንግድ ደረጃ እና ተቀራራቢ ብዛት መሠረት ያደረገ የዋጋ ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው።

d) Adjustments for differences in commercial level or quantity under this article are made only if the evidence provided by the declarant demonstrates that the price difference is due to the seller's commercial level or quantity.

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ላይ ለተጠቀሱ ማስተካከያው ሲደረግ በተጨማሪ የግብይት ዋጋው በአዋጅ አንቀጽ 96/1/ የተጠቀሱት ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዝ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና አንድ ዓይነት የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረጉትን የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማውረድ የአያያዝ የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት።

3) When making adjustments under sub-article (2), if the transaction value includes costs specified in Article 96(1), differences in transportation mode or distance must be considered, including costs for transport, loading, unloading, handling, and insurance up to the customs territory entry point.

4) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክሌር ያደረገው የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ ተቀባይነት ካላገኘ በኮሚሽኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት

4) If the declared value of identical goods is not accepted, the customs value is determined by comparing it with the value of identical

ከሚገኘው የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋን በማነፃፀር ይወሰናል።

goods in the Commission’s customs value database.

5) የዕቃዎች ማነጻጸሪያ ዋጋ በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነጻጸሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው ወደ አገር የገባበት ብዛት እና የተሸጠበት የንግድ ደረጃ ታሳቢ ተደርጎ ዋጋ ከሚወሰንለት ዕቃ ወደ ሀገር ከመግባቱ አስቀድሞ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር ከገባ ዕቃ ዋጋ አነስተኛው ተወስዶ ዋጋው የሚወሰን ይሆናል።

5) If multiple comparable values exist in the database, the customs value is determined by selecting the lowest value of identical goods imported within the 30 days prior to the goods’ entry, considering the quantity and commercial level of the sale.

## 9. የተመሳሳይ ዕቃ የግብይት ዋጋ አወሳሰን ዘዴ

## 9. Transaction Value of Similar Goods

1) የዕቃው ዋጋ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 8 መሰረት ሊወሰን ካልተቻለ በአዋጁ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሠረት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክሌር ያደረገው ዕቃ ከመግባቱ በፊት በነበሩ 90 ቀናት ውስጥ በተመሳሳይ የንግድ ደረጃ እና በተቀራራቢ ብዛት ወደ ሀገር ገብተው በነበሩ ግንኙነት በሌላቸው ገዢዎች የተሸጠ የተመሳሳይ ዕቃን አስመልክቶ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሚያቀርበው የዋጋ መረጃ በመነሳት የዋጋ ውሳኔ ይተላለፋል።

1) If the value of the goods cannot be determined based on Articles 5 and 8 of this directive, the transaction value shall be determined as per Article 92 of the Proclamation, based on the price information provided by the declarant for identical goods sold to unrelated buyers at the same commercial level and in comparable quantities, within 90 days before the importation of the goods in question.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/መሠረት የግብይት ዋጋን መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት፡-

2) If the transaction value cannot be determined under sub-article (1) of this article, as per Article 92, sub-article (2) of the Proclamation:

ሀ/ ተመሣሣይ ንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ፣

a) Goods at the same commercial level but not sold in comparable quantities,

ለ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ወይም

b) Goods at a different commercial level but sold in comparable quantities, or

ሐ/ ተመሣሣይ ያልሆነ የንግድ ደረጃ ያላቸውና በተቀራራቢ ብዛት ያልተሸጡ ተመሳሳይ ዕቃዎችን የንግድ ደረጃው ወይም የብዛት ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተመሣሣይ ዕቃን የግብይት ዋጋ አድርጎ መጠቀም ይቻላል።

c) Goods at a different commercial level and not sold in comparable quantities, can be used to determine the transaction value of identical goods imported into the country by making adjustments for differences in commercial level or quantity that affect the price.

መ/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ደረጃ እና ተቀራራቢ ብዛት ለሚያስከትለው ልዩነት ማስተካከያ የሚደረገው በዲክለራሲዮን አቅራቢው የሚቀርበው ማስረጃ በሻጩ የንግድ ደረጃ እና ተቀራራቢ ብዛት መሠረት ያደረገ የዋጋ ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው።

d) Adjustments for differences in commercial level and comparable quantities under this article shall only be made based on evidence provided by the declarant, demonstrating that the price difference is due to the seller's commercial level and comparable quantities.

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተጠቀሱት ማስተካከያዎች ሲደረጉ የግብይት ዋጋው በአዋጁ አንቀጽ 96 /1/ የተጠቀሱትን ወጪዎች በተጨማሪነት የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣው ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ ወጪ የተደረጉትን የማጓጓዣ፣ የማስጫኛ፣ የማውረጃ፣ የመንከባከቢያ እና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት።

3) When adjustments specified in sub-article (2) of this article are made, if the transaction value includes the costs outlined in Article 96(1) of the Proclamation, it must account for differences related to distance and mode of transport. This includes costs for transportation, loading, unloading, handling, and insurance incurred to deliver the identical goods to the customs territory entry point.

4) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክሌር ያደረገው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ የዕቃው ዋጋ በኮሚሽኑ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት ከሚገኘው የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ ጋር በማነፃፀር የሚወሰን ይሆናል።

4) If the price of identical goods declared by the declarant is not accepted, the value of the goods shall be determined by comparing it with the price of identical goods available in the Commission's customs valuation database.

5) የዕቃዎች በማነጻጸሪያ ዋጋ መረጃ ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነጻጸሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው ወደ አገር የገባበት ብዛት እና የተሸጠበት

5) When two or more prices are available in the comparative pricing data, the customs value shall be determined by considering the

የንግድ ደረጃ ታሳቢ ተደርጎ ዋጋ ከሚወሰንለት ዕቃ ወደ ሀገር ከመግባቱ አስቀድሞ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር ከገባ ዕቃ ዋጋ አነስተኛው ተወስዶ ዋጋው የሚወሰን ይሆናል።

quantity and commercial level at which the goods were sold. The lowest price of identical goods imported within 30 days prior to the importation of the goods in question shall be used to determine the value.

## 10. ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ አፈጻጸም

## 10. Deductive Valuation Method

1) የዕቃው ዋጋ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 8 እና 9 መሰረት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 93 በተደነገገው መሠረት የዕቃዎችን ዋጋ በሚሰላበት ጊዜ ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል በተደረገ ግብይት በዲክላራሲዮን አቅራቢው ወይም በሌሎች ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ዕቃው በተጫነበት አገር በቀጥታ ወይም ከሌላ አገር ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወይም ወደ አገር ውስጥ ከገባ 90 ቀናት ያልበለጠው አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጠበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመስረት እና በአዋጁ የጠቀሱት ዝርዝር ወጪዎችና የትርፍ መጠን ከመሸጫ ዋጋው ላይ በመቀነስ ይወሰናል።

1) If the value of goods cannot be determined under Articles 5, 8, and 9 of this directive, the value is calculated per Article 93 of the Proclamation. It is based on the unit price at which the goods, or identical/similar goods, are sold in the greatest quantity in the importing country within 90 days of importation, in a transaction between unrelated buyers and sellers. This is adjusted by deducting specified costs and profit margins outlined in the Proclamation.

2) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል "ሻጭ' ማለት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ወይም ሌሎች ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች ሲሆን "ገዢ' ማለት ዕቃውን ከዲክላራሲዮን አቅራቢ ወይም ከሌሎች አቅራቢዎች የገዛ ሰው ሲሆን እንደ ሁኔታው አከፋፋይ፣ ቸርቻሪ ወይም የመጨረሻ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

2) For the purpose of this article, "seller" refers to the declaration provider or other providers, and "buyer" refers to the person purchasing from the provider, who may be a distributor, retailer, or end-user, depending on the context.

በዚህ አንቀጽ በተደነገገው ዘዴ መሠረት የጉምሩክ ዋጋ ሊተመን የሚችለው፡-

3) The customs value can be determined by the method stipulated under this article if:

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ 90 በተደነገገው መሰረት በዲክላራሲዮን አቅራቢው /ሻጩ/ እና በገዢው መካከል ግንኙነት ከሌለ ወይም ግንኙነቱ በመሸጫ ዋጋው ላይ ተጽዕኖ እንዳላሳደረ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ፣

a) Pursuant to article 90 of the proclamation, there is no relationship between the declaration provider (seller) and the buyer, or the provider proves the relationship does not affect the sale price.

ለ/ በገዢ በኩል ለሻጩ፡ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ክፍያ ወይም የተሰጠ ስጦታ ከሌለ፣ እና

b) The buyer has not paid or provided any free/discounted payment or gift related to the goods, directly or indirectly, to the seller.

ሐ/ ዕቃው በከፍተኛ ብዛት በአገር ውስጥ የተሸጠበት ነጠላ ዋጋ መሆኑን በማስረጃ ማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ነው።

c) It can be proven that the unit price reflects the highest quantity sold in the importing country.

4) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የዕቃው ዋጋ የሚሰላው ከዚህ በታች የተገለጹትን ቀመሮች ማሰረት በማድረግ ይሆናል።

4) The value of goods is calculated using the formulas specified below:

ሀ/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በገባበት ሁኔታ የተሸጠ የጉምሩክ ዋጋው እንደሚከተለው ይሰላል።

a) For goods imported and sold in the same condition, the customs value is calculated as follows.

1. DPV (Customs Value CIF in ETB) = DMP – (CPS + DGEx + TDT)

1. DPV (Customs Value CIF in ETB) = DMP – (CPS + DGEx + TDT)

2. FOB Price (in USD) = DPV (CIF in USD) - IFO

2. FOB Price (in USD) = DPV(CIF in USD) – IFO

ለ/ ወደ አገር ውስጥ የገባው ዕቃ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ከገባ በኋላ ቀጣይ የምርት ሂደት ተከናውኖበት የተሸጠ እንደሆነ የጉምሩክ ዋጋው በሚከተለው ሁኔታ ይሰላል፤

**b)** The customs value of an item imported into the country, which is identical or similar to an item that undergoes further production processes after importation and is then sold, shall be calculated as follows:

1. DPV (in ETB) = DMP – (CPS + DGEx + TDT + DVA)

1.) DPV (in ETB) = DMP – (CPS + DGEx + TDT + DVA)

2. FOB price (in USD) = DPV (CIF in USD) - IFO

2. FOB price (in USD) = DPV (CIF in USD) – IFO

**መፍቻ**

**Key**

DPV = የቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ

DPV = Duty Paying Value – Customs Value

DMP = የሀገር ውስጥ ገበያ መሸጫ ነጠላ ዋጋ

DMP = Domestic Market Selling Unit Price

FOB = የዕቃ ዋጋ እስከ ወደብ ድረስ

FOB = Free on Bord

| | |
|---|---|
| CIR = የዕቃ ዋጋ፣ የማጓጓዣ ወጪ እና የኢንሹራንስ አረቦን ወጪ | CIR = Cost, (Freight and Insurance) |
| CPS = ከሽያጭ የተገኘ ኮሚሽን ወይም ትርፍ መጠን | CPS = Commission or Profit from Sale |
| DGSx = ሀገር ውስጥ የሚከፈሉ አጠቃላይ ወጪዎች መጠን | DGSx = Domestic General Expenses |
| TDT = አጠቃላይ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ መጠን | TDT = Total Customes Duties and Taxes |
| DVA = ዕቃው አገር ውስጥ ከገባ በኋላ በምርት ሂደት የተገኘ ተጨማሪ እሴት መጠን | DVA = Domestic Value Additions |
| IFO = ዕቃው አገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት የተከፈለ የኢንሹራንስ፣ የመጓጓዣ ወጪ እና ሌሎች ወጪዎች መጠን | IFO = Insurance, Freight and other Costs |
| ETB = Ethiopian Birr | ETB = Ethiopian Birr |

## 11. በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ

1) የዕቃው ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 94 በተደነገገው መሠረት ለማስላት በዕቃው ዋጋ የሚካተቱ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ክፍያዎችና ወጪዎችን ከአምራቹ ድርጅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚገኙ መረጃዎች እና ደጋፊ ማስረጃዎች በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል።

2) በአዋጁ አንቀጽ 94 መሠረት ለመወሰን በላኪው ሀገር ተቀራራቢ የዕድገት ደረጃ ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም በዕቃው ንግድ ዘርፉ አብዛኛውን ጊዜ ያለው የተለመደ ወይም አማካይ የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ ሊወሰን ይችላል።

## 11. Computed Valuation Method

1) The value of the goods, as per Article 94 of the Proclamation, can be determined based on the payments made or to be made for the goods, including costs and expenses, using information and supporting evidence obtained directly or indirectly from the manufacturer's organization.

2) In accordance with Article 94 of the Proclamation, the valuation can be determined based on evidence of the typical or average selling, packaging, and other costs, as well as the profit margin, commonly observed in the exporting country for similar goods at a comparable level of development when sold by manufacturers or in the trade sector of the goods.

## 12. ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ

የዕቃዎች ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 94 በተደነገገው የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እስከ 11 የተጠቀሱትን የዋጋ ትመና ዘዴዎችን በቅደም ተከተላቸው አተረጓጐማቸውን በማስፋት በአዋጁ ከተደነገገው አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣማ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ወቅታዊ መረጃ መሰረት ከዚህ በታች በተገለጸው አግባብ ቅደም ተከተል ዋጋ ይወሰናል።

## 12. Fallback Valuation Method

When the value of goods cannot be determined using the valuation method specified in Article 94 of the Proclamation, the balanced valuation method is applied in accordance with Articles 8 to 11 of this directive, in their sequential order, consistent with the general principles of the Proclamation. The value is determined based on current data in Ethiopia, following the sequence below:

### 1) የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ሚዛናዊ ዘዴ

ሀ/ በ90 ቀናት ውስጥ የገባ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ወቅት በ180 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር የገባ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ እንደ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ሊያገለግል ይችላል።

ለ/ የዕቃዎች ማነጻጸሪያ ዋጋ በመረጃ ሥርዓት ሁለትና ከዚያ በላይ በሚገኝበት ወቅት የጉምሩክ ዋጋ ማነጻጸሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው ወደ አገር የገባበት ብዛት እና የተሸጠበት የንግድ ደረጃ ታሳቢ ተደርጎ ዋጋ ከሚወሰንለት ዕቃ ወደ ሀገር ከመግባቱ አስቀድሞ ባሉት 60 ቀናት ውስጥ ወደ ሀገር ከገባ ዕቃ ዋጋ አነስተኛው ተወስዶ ዋጋው የሚወሰን ይሆናል።

ሐ/ ወደ አገር የገባው ዕቃ በተመረተበት አገር የተመረተ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ በማይገኝበት ጊዜ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ በሚገኝ አገር የተመረተ የአንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ አድርጐ መውሰድ ይችላል።

### 1) Identical or Similar Goods Fallback Value Method

a) If the value of identical or similar goods imported within 90 days is unavailable, the value of identical or similar goods imported within 180 days may be used as the basis for customs and tax valuation.

b) When comparative price data for goods is available in the information system (two or more sources), the customs value is determined by comparing the quantity of goods imported and the commercial level at which they were sold. The lowest value of identical or similar goods imported within the previous 60 days is used.

c) If the value of identical or similar goods produced in the country of origin is unavailable, the value of identical or similar goods produced in a country at a similar level of development may be used.

መ/ ወደኋላ በማስላት እና በወጪ ስሌት ላይ በተመሰረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሰረት የተወሰኑ የአንድ አይነት ዕቃ ወይም የመሳሳይ ዕቃ ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፊያ ዋጋ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

d) The value of identical or similar goods, determined through backward calculation or cost-based valuation methods, may serve as the basis for customs and tax valuation.

ሠ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት ውሳኔ መስጠት ካልተቻለ ለተጨማሪ 180 ቀናት ውስጥ ብቻ ያለ መረጃ በቅደም ተከተል በመውሰድ ዋጋ መወሰን ይቻላል።

e) If a decision cannot be made under point (a), the value can be determined using available data within an additional 180 days, following the sequential order.

**2) ወደኋላ የማስላት ሚዛናዊ ዘዴ**

**2) Deductive Fallback Value Method**

ሀ/ በብዛት የተሸጠበት ዋጋ ካልተገኘ በነጠላ የተሸጠበትን አማካኝ ዋጋ እንደ መነሻ በመውሰድ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ /ለ/ በተቀመጠው ቀመር መሰረት አስፈላጊውን ተቀናሾች በመቀነስ የጉምሩክ ዋጋ ይሰላል፣

a) If the price at which the goods are most commonly sold is not available, the average price of individual sales is taken as the basis, and the customs value is calculated by deducting the necessary deductions according to the formula specified in this article, paragraph (b).

ለ/ ተጨባጭና ሊለኩ የሚችሉ መረጃዎች ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ ቀጥሎ ያሉትን ቀመሮች እንደ ቅደም ተከተላቸው በመጠቀም የCIF እና የFOB ዋጋን መወሰን ይቻላል

b) When tangible and measurable data cannot be obtained, the CIF and FOB values can be determined by using the subsequent formulas in their respective order.

1. $\text{DPV (in ETB)} = \frac{\mathbf{DMP\ (1-pfm-exp)}}{1+\sum(\mathbf{Tax\ Rates})}$

2. FOB price (in USD) = DPV (CIF in USD) – IFO

$\text{DPV (in ETB)} = \frac{\mathbf{DMP\ (1-pfm-exp)}}{1+\sum(\mathbf{Tax\ Rates})}$

2. FOB price (in USD) = DPV (CIF in USD) – IFO

**መፍቻ፡-**

DPV = የቀረጥና ታክስ ማስከፊያ ዋጋ

DMP = የሀገር ውስጥ ገበያ መሸጫ ነጠላ ዋጋ

FOB = የዕቃ ዋጋ እስከ ወደብ ድረስ

CIF = የዕቃ ዋጋ፣ ማጓጓዣ ወጪ እና የኢንሹራንስ አረቦን ወጪ

**Key**

DPV = Duty Paying Value –Customs Value

DMP = Domestic Market Selling Unit Price

FOB = Free on Bord

CIF = Cost, Freight and Insurance

PFM = ከዕቃው ጠቅላላ ሽያጭ የሚገኝ የትርፍ ምጣኔ በመቶኛ

PFM = Percentage rate of Usual Commissions or profits from sale of such goods

EXP = ከዕቃው ጠቅላላ ሽያጭ ታሳቢ የሚድረግ አጠቃላይ የወጪ ምጣኔ በመቶኛ ለዕቃው የሚከፈለው ጠቅላላ የቀረጥና ታክስ ምጣኔ ስሌት

EXP = percentage rate of usual domestic general expenses in sale of such goods) tax rates cumulative Summation

CIR in USD = ሲከፈል በወቅቱ ባለው የገንዘብ ምንዛሬ መጠን

CIR in USD = CIF in ETB

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ለ/ /2/ በተመለከተው ቀመር መሠረት የCIF ዋጋን ለማግኘት የገበያ ጥናት ከተገኘው የመሸጫ ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡-

c) Based on the formula stipulated under sub article b/2 above, the following costs are deducted from the market sale price (obtained through market research), to determine the CIF price:

1) ዕቃውን ለመሸጥ የተከፈለ ኮሚሽን ወይም የሚከፈል፣ ትርፍ እና ዕቃውን ለመሸጥ የወጣ ጠቅላላ ወጪ፣

1) Any commission paid for selling the goods, profit, and total expenses incurred in the sale.

2) ዕቃው አገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተከፈሉ ተጨማሪ ወጪዎችና ክፍያዎች፣

2) Expenses and fees incurred after the goods enter the country.

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ለ/ በተመለከተው ቀመር መሰረት የተገኘውን የFOB ዋጋ ከኢንቮይስ የFOB ዋጋ ለማነፃፀር ዲክላራሲዮን አቅራቢው እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለኢንሹራንስ፣ ማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ እና የመንከባከቢያ ወጪዎች የተከፈለበትን ማስረጃ ካላቀረበ ወይም ተቀባይነት ካላገኘ በቀመሩ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 96 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት የኢንሹራንስ ወጪ፣ የትራንስፖርት ወጪ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ እና የመንከባከቢያ ወጪዎች በመቀነስ ማስላት ይቻላል።

d) To compare the FOB price calculated based on the formula specified in this article, sub-article, letter /b/ with the FOB price on the invoice, if the declarant fails to provide evidence of payment for insurance, transportation, loading, unloading, and handling costs up to the first port of entry in Ethiopia, or if such evidence is not accepted, the insurance costs, transportation costs, loading, unloading, and handling costs can be deducted and calculated in accordance with Article 96 of the Proclamation and Article 14 of this Directive

ሠ/ የገበያ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል።

e) During market research, the following specific conditions will be taken into account.

1) ለማነፃፀሪያ የሚወሰደው ዕቃ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ እቃ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1) Ensure that the item used for comparison is of the same or similar type.

2) ዕቃው በአገር ውስጥ ሲሸጥ ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ይዘት መሆን ያለበት ሲሆን ተጨማሪ እሴት የታከለበት እንደሆነ ይህንኑ መጠን በተጨባጭ ማስረጃ ሊታወቅ ይገባል፣

2) The item must be in the same condition as when it entered the country when sold domestically, and any added value must be verifiable with tangible evidence.

3) በአገር ውስጥ ሲሸጥ ግንኙነት በሌላቸው ገዢና ሻጭ መካከል የተደረገ ግብይት መሆን አለበት፣

3) The domestic sale must be a transaction between unrelated buyers and sellers.

4) ዕቃዎች በከፍተኛ ብዛት በሀገር ውስጥ በተሸጡበት የጅምላ ወይም ነጠላ ዋጋ ላይ የመሰረተ መሆን ይኖርበታል፣

4) The item's price must be based on the wholesale or retail price at which it is sold in large quantities domestically.

5) ዕቃው የተሸጠበት ጊዜ ዕቃው በገባበት ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፣

5) The time of the item's sale must be close to or concurrent with the time it entered the country.

6) በገዢው በኩል ለሻጩ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ በነፃ በቅናሽ ዋጋ የተከፈለ ወይም የተሰጠ ስጦታ መኖር የለበትም።

6) There should be no free or discounted goods, services, or gifts provided by the buyer to the seller, directly or indirectly, related to the item.

7) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለዕቃው፣ ለአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የተሸጠበትን የጅምላ ወይም የችርቻሮ ዋጋ በደረሰኝ የሚያቀርብ ከሆነ እና የቀረበው ደረሰኝ በትክክል የተሸጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ ገበያ ከማጥናት ይልቅ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደመነሻ ይወሰዳል።

7) If the declaration provider submits a receipt for the wholesale or retail price of the item or a similar item, and the receipt is verified as accurate, it should be prioritized as the basis instead of conducting a market study.

8) ጥናቱን የሚያደርገው ቅ/ጽ/ቤት ወይም የሥራ ክፍል ዕቃው በብዛት የሚሸጥበትን ወይም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን ቦታ ለይቶ ማጥናት አለበት።

8) The department or unit conducting the study must identify and examine the location where the item is commonly sold or used.

9) ዕቃው በብዛት የሚሸጥበት የገበያ አካባቢን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት።

9) The study must focus on the market area where the item is predominantly sold.

10) ብዛት ያላቸው የተለያዩ አማራጭ ገበያዎች የሚገኙ ከሆነ የገበያ ጥናቱ የመጨረሻ አማካይ ውጤት ከመወሰዱ በፊት ዕቃው ቢያንስ ከሶስት ዕቃው በብዛት የሚሸጥበት ገበያ ወይም ድርጅቶች ተጠይቆ በብዛት የሚሸጥበትን አማካይ የዋጋ መረጃ መወሰድ አለበት።

10) If multiple alternative markets are available, the market study must collect average price data from at least three markets or entities where the item is commonly sold before determining the final average result.

ረ/ የገበያ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ጥናቱን የሚያደርገው የሥራ ክፍል በዚህ መመሪያ አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ቅጽ የተመለከቱትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ጥናቱን ማከናወን ይኖርበታል።

f) During a market study, the department conducting the study must carry it out based on the requirements specified in the attached/annexed form, in accordance with this guideline.

ሰ/ ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ በተጠቀሰው የወደ ኋላ ሚዛናዊ ዘዴ በመጠቀም ያስተላለፈው ውሳኔ ውሳኔውን በተሰጠበት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ከዝርዝር ማስረጃዎቹ ጋር ለዳይሬክቶሬቱ ማሳወቅ አለበት፣

g) The Customs Office must notify the Directorate of its decision, made using the retrospective valuation method specified in this article, within five consecutive working days, along with detailed evidence.

### 3) ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን

### 3) Valuation of goods made from Composite materials

ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃ ሆነው ቅ/ጽ/ቤቱ የጉምሩክ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ በሁሉም የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በመጠቀም ውሳኔ መስጠት በማይችልበት ጊዜ የዕቃውን የጉምሩክ ዋጋ ለመወሰን ዕቃው የተሰራበት የድብልቅ ንጥረ ነገሮች ዋጋ ተወስዶ አማካይ ሬሾ ላይ በመመስረት ይሆናል።

If the imported goods are made from mixed materials and the Customs Office’s expert or responsible officer cannot determine the value using all valuation methods, the customs value of the goods will be determined based on the value of the mixed components, using an average ratio.

## ምዕራፍ ሁለት

## Chapter Two

## በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ስለሚጨመሩ፣ ስለሚቀነሱ እና የማይካተቱ ክፍያዎችና ወጪዎች አጠቃላይ አፈጻጸም ሂደት

## General Implementation Procedures for Costs and Payments Included, Excluded,

**or Deducted in the Customs Duty and Tax Assessment Value**

**13. በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ስለሚካተቱ ተጨማሪ ክፍያዎችና ወጪዎች**

**13. Additional Costs and Payments Included in the Customs Duty and Tax Assessment Value**

በአዋጁ አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት እቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ ለዕቃው የተከፈሉ ወይም የሚከፈሉ ወጪዎችና ክፍያዎች በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መካተት አለባቸው፡:

As stipulated in Article 96 of the Proclamation, all costs and payments paid or payable for the delivery of goods up to the first point of entry into Ethiopia must be included in the customs duty and tax assessment value.

**14. ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ የሚካተቱበት ሁኔታ**

**14. Conditions for Including Additional Payments in the Transaction Value of Goods**

1) በአዋጁ አንቀጽ 96 በተደነገገው መሠረት ተጨማሪ ወጪዎችና ክፍያዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ይካተታሉ፡-

1) As stipulated in Article 96 of the Proclamation, additional costs and payments are included in the following circumstances:

ሀ/ በኢንቮይሱ እና ሌሎች የንግድ ሰነዶች ላይ በግልጽ የተካተቱ ስለመሆናቸው ያልተገለጸ ከሆነ፣ ወይም

a) If they are not explicitly stated in the invoice or other commercial documents, or

ለ/ የተከፈለው የዕቃው ዋጋ በንግድ ሰነድ ላይ በትክክል ያልተገለፀ ከሆነ፣ ወይም

b) If the paid value of the goods is not accurately specified in the commercial documents, or

ሐ/ ዋጋ ሊተመንበት ከቀረበው ዕቃ ጋር በተያያዘ የተከፈለ ሲሆን፣ ወይም

c) If they are paid in connection with the goods for which the value is to be assessed, or

መ/ ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበላቸው ከሆነ ነው።

d) If clear information is provided regarding their payment.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጨማሪ ክፍያዎች በዕቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ እንዲካተቱ ሲደረግ:-

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, additional fees shall be included in the customs duty and tax assessment value of the goods as follows:-

ሀ/ ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ በትክክል የተከፈሉት ወይም የሚከፈሉት ወጪዎችና ክፍያዎች በአስመጪው እንዲቀርብ በማድረግ እንዲካተት ይደረጋል።

a) Costs and payments actually paid or payable for delivering the goods up to the first point of entry into Ethiopia shall be presented by the importer for inclusion.

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የክፍያ ማስረጃ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ወይም በተለያዩ አሳማኝ ምክንያት መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ በተመሳሳይ ጊዜ ከተመሳሳይ ሀገር የገባን አንድ አይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ ለማጓጓዝ የተከፈለ ወጪ መሠረት ይወሰናል።

b) Based on sub-article 2(a) of this article, the proof of payment provided by the declarant shall be deemed acceptable, or if it cannot be provided for convincing reasons, it shall be determined based on the costs paid for transporting identical or similar goods imported from the same country at the same time.

ሐ/ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ከጐረቤት ሀገራት ወደቦች እስከ መድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ላለው ርቀት የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከወደብ እስከ መግቢያ በር ያለው ርቀት ከወደብ እስከ መድረሻ ጣቢያው ላለው ርቀት ተካፍሎ የሚገኘው ውጤት ጠቅላላ በተከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ተባዝቶ የሚገኘው ውጤት ነው።

c) For goods imported from neighboring countries' ports to the destination customs station, the transport cost paid for the distance from the port to the entry gate shall be multiplied by the total transport cost, proportional to the distance from the port to the destination station.

መ/ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የሮያሊቲ ክፍያ የሚፈፀምበት ሆኖ ሲገኝ ክፍያው አስመጪው ከላኪው ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ወይም በተሸጠ ጊዜ የሚፈፀም ይሆናል።

d) For goods imported into the country subject to royalty payments, the payment shall be made based on the agreement between the importer and the exporter, either upon entry into the country or at the time of sale.

ሠ/ የሮያሊቲ ክፍያው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ያልተከፈለ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ፊደል ተራ /መ/ መሰረት መከፈል

e) If the royalty payment has not been made upon the goods' entry into the country, as per sub-article 2(d) of this article, the importer

ያለበትን የሮያሊቲ ክፍያ የዕቃው ሽያጭ በተከናወነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስመጪው አሳውቆ መክፈል አለበት።

must notify and pay the royalty payment within one month of the sale of the goods.

ረ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ /መ/ እና /ሠ/ የተመለከተው ቢኖርም በሮያሊቲ ክፍያ ላይ ቀረጥና ታክስ ያልከፈለ አስመጪ ዕቃው ወደ አገር ውስጥ በገባ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት።

f) Notwithstanding sub-articles 2(d) and 2(e) of this article, an importer who has not paid duties and taxes on royalty payments must settle the duties and taxes within one year of the goods' entry into the country.

ቀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃ መሠረት መተመን ባልታቻለ ጊዜ ኮሚሽኑ ወጪዎችንና ክፍያዎችን አግባብነት ካላቸው ከመንግስትና የግል መ/ቤቶች በሚያገኘው መረጃ መሰረት ዋጋ ሊተምን ይችላል።

g) Based on sub-article 2(a) of this article, as per the Proclamation and this directive, if the fees added to the customs duty and tax assessment value cannot be assessed based on tangible evidence, the Commission may determine the value of costs and fees based on information obtained from relevant government and private institutions.

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ መተመን ባልተቻለበት ጊዜ ኮሚሽኑ ተጨማሪ ወጪዎችን ሌሎች ተቀባይነት ባላቸው ዘዴዎች ይወስናል።

3) If additional payments cannot be assessed based on tangible information and evidence as per sub-articles 1 and 2 of this article, the Commission shall determine the additional costs using other acceptable methods.

4) በጎረቤት አገር ተመርቶ ወደ አገር የሚገባ ዕቃ ዋጋ ላይ ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ በትክክል የተከፈለ የየብስ ትራንስፖርት እና ኢንሹራንስ ወጪን ብቻ በማካተት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚሰላ ይሆናል።

4) For goods produced in a neighboring country and imported into Ethiopia, the customs duty and tax assessment value shall be calculated by including only the actual land transport and insurance costs paid to deliver the goods to the first point of entry into Ethiopia's customs territory.

5) ከስሪት አገራቸው ውጭ ከጐረቤት አገሮች የሚከናወኑ ግዥዎችን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

5) For purchases conducted from neighboring countries outside their country of origin, the provisions of Article 20 of this directive shall apply.

## 15. በግብይት ዋጋ የማይካተቱ ክፍያዎች

## 15. Payments Not Included in the Transaction Value

1) ለዕቃው በትክክል የተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ውስጥ ተለይተው እስከተቀመጡ ድረስ የሚከተሉት ክፍያዎች በግብይት ዋጋ ውስጥ አይካተቱም፤

1) The following payments, provided they are separately identified in the actual or payable value of the goods, shall not be included in the transaction value:

ሀ/ የማምረቻ መሳሪያዎችን ወይም ማሽነሪዎች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለተከናወነ ወይም ለሚከናወን የግንባታ፣ የማሻሻያ፣ የተከላ ወይም የጥገና ሥራ ወይም ለቴክኒክ ድጋፍ የሚከፈል ክፍያ፤

a) Payments paid for construction, modification, installation, maintenance work, or technical support performed or to be performed after the importation of production equipment or machinery into the country;

ለ/ ዕቃው ወደ ጉምሩክ ክልል ከገባ በኋላ የሚከፈል የትራንስፖርት ክፍያ፤

b) Transport fees paid after the goods have entered the customs territory;

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ ከገባ ዕቃ ግዥ ጋር በተያያዘ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለገባው የፋይናንስ ስምምነት የሚከፈል የወለድ ክፍያ፤

c) Interest payments made by the declarant for financial agreements related to the purchase of goods imported into the country;

መ/ የግዢ ኮሚሽን፤

d) Purchase commissions;

ሠ/ ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈለ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች።

e) Duties, taxes, and other payments paid within Ethiopia in connection with imported goods.

2) የግብይት ዋጋ ሲወሰን የሚከተሉት ክፍያዎች ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ አይደመሩም፤

2) When determining the transaction value, the following payments shall not be added to the actual or payable value of the goods:

ሀ/ ወደ አገር ውስጥ የገባን ዕቃ በአገር ውስጥ እንደገና ለማምረት የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

a) Payments paid for reprocessing imported goods within the country;

ለ/ ዕቃውን ለመላክ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃን ለማከፋፈል ወይም እንደገና ለመሸጥ በገዢው የሚከፈሉ ክፍያዎች።

b) Payments paid by the buyer for distributing or reselling imported goods, unless pre-conditioned for export.

16. ከግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሳቦች

**16. Deductions from the Transaction Value**

1) ወደ አገር ውስጥ ከሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፡-

1) The following amounts shall be deducted from the transaction value of goods imported into the country:

ሀ/ ዕቃ በጉዞ ላይ ሳሉ የደረሰ ጉዳት በሚመለከተው ህጋዊ አካል ማስረጃው ተረጋግጦ ሲቀርብ፤

a) Damages to goods during transit, provided evidence is verified and submitted by the relevant legal entity;

ለ/ ዕቃ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሳለ የደረሰ ጉዳት በሚመለከተው ህጋዊ አካል ማስረጃው ተረጋግጦ ሲቀርብ፤

b) Damages to goods while in a customs warehouse, provided evidence is verified and submitted by the relevant legal entity;

ሐ/ አደገኛ በመሆኑ ምክንያት በአዋጁ መሰረት እንዲወገድ የተደረገ ዕቃ ዋጋ።

c) The value of goods ordered to be removed due to their hazardous nature, as per the Proclamation.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ /1/ የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው አስፈላጊ ማስረጃዎችን ከዲክላራሲዮን ጋር አያይዞ ለኮሚሽኑ ሲያቀርብና እና ትክክለኛነቱ ሲረጋገጥ ይሆናል።

2) The provisions of sub-article (1) of this article shall apply when the declarant submits the necessary evidence along with the declaration to the Commission and its accuracy is verified.

## ምዕራፍ ሶስት

## የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት

## Chapter Three

## Customs Valuation Information System

17. የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ስርዓት አጠቃቀም

**17. Use of the Customs Valuation Information System**

ኮሚሽኑ፡-

The Commission:

1) አስቀድሞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ዋጋን መነሻ በማድረግ በስጋት ስራ አመራር መርህ መሰረት ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችለውን የዕቃ ዋጋ መረጃን ያደራጃል፤

1) Shall organize price information for previously imported goods to serve as a basis for risk management operations.

2) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክለኛ የግብይት ዋጋ ስለመሆኑ ለማጣራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)

2) Shall utilize the price information organized under sub-article (1) of this article to verify whether the value of goods declared

መሰረት የተደራጀውን የዋጋ መረጃን ጥቅም ላይ ያውላል።

by the declarant represents the accurate transaction value.

3) ከዋጋ አተማመን ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸው የመንግስት እና ሌሎች ተቋማት ጋር እንደ አስፈላጊነቱ የመረጃ ልውውጥ ሊያደረግ ይችላል።

3) May exchange information with relevant government and other institutions as necessary in connection with valuation.

4) በዚህ አንቀጽ የተደራጀውን የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓትን መጠቀም የሚቻለው በኮሚሽኑ የይለፍ ቃል ሲሰጥ ብቻ ነው።

4) The customs valuation information system organized under this article may only be accessed with a password provided by the Commission.

## 18. የጉምሩክ ዋጋን ስለማልማት

## 18. Development of Customs Valuation

1) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለስጋት ሥራ አመራር እና ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የዕቃ የማነፃፀሪያ ዋጋን በየወቅቱ ያደራጃል፤ ሥራ ላይ ያውላል።።

1) Subject to the provisions of the Proclamation and this directive, the Commission shall periodically organize and utilize a reference price for goods for risk management and post-clearance audits.

2) ኮሚሽኑ ከታወቁ ዓለም አቀፍ የዕቃ ዋጋ አቅራቢ ድርጅቶች ወይም ከተመረጡ ዓለም አቀፍ የዋጋ መረጃ ምንጮች ወይም ከተመረጡ ድረ-ገጾች ወይም ከሀገራት ጋር በሚኖር የዕቃዎች ዋጋ መረጃ ልውውጥ ስምምነት ወይም ከሌሎች ተኣማኒ የዕቃ ዋጋ መረጃ ምንጮች በግዥ ወይም በሌሎች መንገዶች የዋጋ መረጃ ሥርዓቱን ያለማል፤ ይወስናል።

2) The Commission shall develop and determine the price information system by obtaining data from recognized international price provider organizations, selected international price information sources, selected websites, agreements for exchanging price information with other countries, or other reliable sources through purchase or other means.

3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚለማው የጉምሩክ የዕቃዎች ዋጋ መረጃ እንደማነፃፀሪያ ዋጋ ሆኖ ያገለግላል።

3) The customs valuation data developed under this article shall serve as a reference price.

4) ኮሚሽኑ የሚደራጀውን የዕቃዎች የማነፃፀሪያ ዋጋ የዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ የመነሻ ዋጋ አድርጎ መጠቀም የሚችለው የዕቃዎቹ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ

4) The Commission may use the organized reference price for goods as the initial customs duty and tax assessment value,

የመነሻ ዋጋ በኮሚሽነሩ ተወስኖ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ቋት ላይ ተጭኖ ተፈፃሚ የሚደረግ ነው፤ ይህም የሚሆነው ኮሚሽኑ የተሟላ የዕቃዎች የዋጋ መተመኛ አቅም እስከሚገነባ ጊዜ ድረስ ብቻ ይሆናል።

provided the value is determined by the Commissioner, recorded in the customs valuation database, and applied. This shall only occur until the Commission establishes a comprehensive capacity for goods valuation.

## 19. ከተመረተበት አገር ውጭ ተገዝቶ የሚገባ ዕቃ ዋጋ ስለመወሰን

## 19. Determination of the Value of Goods Purchased and Imported from Outside Their Country of Origin

ከስሪት ሀገራቸው ውጭ ተገዝቶ የሚገባ እቃ ዋጋ ሲወሰን፡-

When determining the value of goods purchased and imported from outside their country of origin:

1) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ከተመረተበት አገር ውጪ ተገዝቶ የገባው ኤፍ.ኦ.ቢ /FOB/ ዋጋ ከተመረተበት አገር ተገዝተው ከገባው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ በማነፃፀሪያ የዕቃ ዋጋ መረጃ ሥርዓት ውስጥ የተያዘው የማነጻጸሪያ የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እኩል ሆኖ ወይም በልጦ ከተገኘ ከተመረተበት አገር ውጭ ተገዝቶ የገባ ኤፍ.ኦ.ቢ /FOB/ ዋጋ እንደ ሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ተደርጎ በመውሰድና እስከ ሀገሪቱ የመግቢያ በር ድረስ ለዕቃው የተከፈለውን የየብስ መጓጓዣ ወጪ በማካተት ሊስተናገድ ይችላል።

1) If the FOB (Free on Board) value of the goods, as declared by the declarant and purchased outside the country of origin, is found to be equal to or higher than the CIF (Cost, Insurance, and Freight) reference value of identical or similar goods recorded in the comparative price information system, the FOB value of the goods purchased outside the country of origin may be treated as the CIF value, and the land transportation costs incurred up to the country's entry gate may be included for processing.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ኤፍ.ኦ.ቢ /FOB/ ዋጋ ከሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር አንሶ ከተገኘ ዕቃው ከተመረተበት አገር ሲገዛ ባለው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የሲ.አይ.ኤፍ /CIF/ ዋጋ መሠረት እንዲስተናገድ ይደረጋል።

2) Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this article, if the FOB value declared by the declarant is found to be lower than the CIF value when compared, the goods shall be processed based on the CIF value of

identical or similar goods purchased from the country of origin.

## ምዕራፍ አራት

## የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ

### 20. የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ አቀራረብ

ማንኛውም ዲክላራሲዮን አቅራቢ በአዋጁ አንቀጽ 10/1/ መሠረት ዕቃን ወደ አገር ውስጥ ሲያስገባ አስፈላጊ መረጃዎችን በዋጋ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ ላይ በትክክል በመሙላትና አባሪ ሰነዶችን ከዲክላራሲዮን ጋር በማያያዝ እንዲሁም ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት።

### 21. በጉምሩክ የዋጋ ዝርዝር መረጃ ዲክላራሲዮን ውስጥ መካተት ያለባቸው መረጃዎች

1) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለዋጋ አወሳሰን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክላራሲዮን በመሙላት ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ስለተፈጸመው ግብይት የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ/ የዲክላራሲዮን አቅራቢውና ላኪን ጨምሮ በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ስምና ዝርዝር መረጃ፣

ለ/ ስለዕቃ የግብይት ሁኔታ፣

## Chapter Four

## Customs Valuation Detail Declaration

### 20. Submission of the Customs Valuation Detail Declaration

Any declarant, when importing a good as per Article 10(1) of the Proclamation, must accurately complete the valuation detail declaration form with the necessary information, attach supporting documents to the declaration, verify their accuracy, and submit them to the Commission when importing goods into the country.

### 21. Information to be Included in the Customs Valuation Detail Declaration

1) The declarant must provide the necessary information for valuation by completing the customs valuation detail declaration and submitting it to the Commission

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following detailed information regarding the transaction:

a) Names and detailed information of the parties involved in the transaction, including the declarant and the exporter;

b) Details of the transaction conditions for the goods;

ሐ/ በገዥና ሻጭ መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታና ዓይነት ዝርዝር፣

c) Details of the nature and type of relationship between the buyer and seller;

መ/ የኢንቮይሱ ዋጋ፣ የምንዛሪ ዓይነት፣ የንግድ ስምምነት ዓይነት (INCOTERMS) ፣

d) Invoice value, currency type, and type of commercial agreement (INCOTERMS);

ሠ/ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች፣

e) Payments made by the declarant, directly or indirectly, in cash or in kind, related to the goods;

ረ/ ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያ፣

f) Payments made or to be made directly related to the goods or associated rights;

ሰ/ ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች፣

g) Other costs incurred to purchase the goods;

ሸ/ ከግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ ውጭ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሌሎች የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን በመተመን ለጉምሩክ ካቀረበ የተጠቀመበትን ዘዴ መግለጽ፤

h) If the declarant uses a valuation method other than the transaction value method, a description of the method used.

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የዕቃውን ዋጋ በአግባቡ ለመተመን እንዲቻል የሚከተሉትን መግለጫና መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

3) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following descriptions and information to accurately value the goods: -

ሀ/ የዕቃውን ሙሉ ስም /የንግድ ሥም ወይም ቴክኒካል ስም/፣

a) Full name of the goods (commercial or technical name);

ለ/ የዕቃው መለኪያ /Standard International Unit of Measurement/ እንደ ኪሎ ግራም፣ ሜትር፣ ሊትር እና የመሳሰሉት፤

b) Measurement of the goods (Standard International Unit of Measurement, e.g., kilogram, meter, liter, etc.);

ሐ/ የዕቃውን አምራች ስም እና የተመረተበት አገር፣ ሐ/ የዕቃውን ተጨማሪ መግለጫ /ለምሳሌ፡- ብራንድ፣ ሞዴል ቁጥር፣ ፓርት ቁጥር፣ መጠን፣ ጉልበት/፣

c) Name of the manufacturer and country of origin; Additional description of the goods (e.g., brand, model number, part number, size, capacity);

መ/ ዕቃው የተሠራበት ማቴሪያል /ከድብልቅ ማቴሪያል የተሠራ ከሆነ የይዘቱ መቶኛ መጠን/፣

d) Material composition of the goods (if made of mixed materials, the percentage content);

ሠ/ የዕቃውን አገልግሎት /ጥቅም/ መግለጫ፣

e) Description of the use or purpose of the goods;

ረ/ የመድኃኒት፣ ኬሚካል ስምና ዝርዝር ቴክኒካል መረጃ የሚያሳይ ሰነድ፣

f) Documents showing the name and detailed technical information for medicines or chemicals;

ሰ/ የተሽከርካሪ ሥም፣ ዓይነት፣ ሞዴል ቁጥር፣ ምርት ዘመን፣ ሞተር ቁጥር፣ ሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር /ሲሊንደር/ ጉልበት፣ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ ሊብሬ/የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/

g) For vehicles: name, type, model number, production year, engine number, chassis number, engine/cylinder capacity, and, if applicable, a title/ownership certificate for used vehicles;

ሸ/ የኤሌክትሮኒክስ፣ የማሽነሪዎችና የመለዋወጫዎች ዝርዝር ማኑዋል እና ቴክኒካል ካታሎግ፣ የማሽነሪ ሴሪያል ቁጥር፣

h) Detailed manuals and technical catalogs for electronics, machinery, and spare parts, including machinery serial numbers;

ቀ/ የመለዋወጫ ዕቃዎች ስም፣ የሚገጠምለት የተሽከርካሪ ዓይነት፣ የአምራች ስም፣ ኦርጅናል ከሆነ ፓርት ቁጥር፣ ኦርጅናል ካልሆነ የዕቃው አምራች ፓርት ቁጠር እና የኦርጅናል ሪፈረንስ /OEM/ ፓርት ቁጥር፣

i) For spare parts: name, type of vehicle they are intended for, manufacturer's name, part number (if original), or manufacturer's part number and original equipment manufacturer (OEM) reference number (if not original);

በ/ የዕቃው ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መግለጫና መረጃዎች፤

j) Other necessary descriptions and information for valuing the goods.

## 22. ከጉምሩክ ዝርዝር የዋጋ መረጃ ዲክላራሲዮን ጋር በአባሪነት ስለሚቀርቡ መረጃዎችና ሰነዶች

## 22. Information and Documents to be Attached to the Customs Valuation Detail Declaration

በአዋጁ ከአንቀጽ 90 እስከ 96 በተደነገገው መሠረት የገቢ ዕቃን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 25 እስከ አንቀጽ 31 የተገለጹትን ዋና ዋና መረጃዎችና ሰነዶችን ጨምሮ ከዕቃ ዲክላራሲዮንና ከዝርዝር የዋጋ መረጃ

To determine the customs duty assessment value of imported goods, as per Articles 90 to 96 of the Proclamation, the key information and documents specified in Articles 25 to 31 of this directive must be submitted to the

ዲክላራሲዮን ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት።

Commission as necessary, along with the goods declaration and the valuation detail declaration.

**23. በግብይት ዋጋ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች**

**23. Information and Documents Required for Processing Based on the Transaction Value**

1) ዲክላራሲዮን አቅራቢው በግብይት ዋጋ መሰረት ለመስተናገድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን ከዲክላራሲዮን ጋር አባሪ በማድረግ ማቅረብ ይኖርበታል።

1) The declarant must submit the necessary information and documents attached to the declaration for processing based on the transaction value.

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ግገር ስለመከናወኑ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

2) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and information to verify the transaction:

ሀ/ የዋጋ ሰነድ /ኢንቮይስ/፣

a) Invoice;

ለ/ በግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ አካላት እና ሚናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ፣

b) Evidence specifying the entities involved in the transaction and their roles;

ሐ/ ገቢ ዕቃዎቹ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከመግባታቸው በፊት ዕቃዎቹን ለመግዛት የተገቡ ውሎችና ሥምምነቶች፣

c) Contracts and agreements entered into for the purchase of the goods before they enter customs control;

መ/ ከዕቃው ግገር ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች /ለምሳሌ፡- የታደሰ የአስመጪነት ፈቃድ፣ የታደሰ የላኪነት ፈቃድ፣ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣ ፓኪንግ ሊስት፣ የሥሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የባንክ ፈቃድ፣ የኢንሹራንስ ደረሰኝ፣ የማጓጓዣ ወይም ማስጫኛ ሰነድና ደረሰኝ፤

d) Other documents related to the purchase of the goods (e.g., renewed import license, renewed export license, proforma invoice, packing list, certificate of origin, bank permit, insurance receipt, transport or loading documents, and receipts).

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለዕቃው የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

3) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and information to verify the accuracy of the paid or payable value of the goods:

| | |
|---|---|
| ሀ/ ከዕቃው ጋር በተያያዘ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብ ወይም በዓይነት የተከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣ | a) Detailed information or documents showing payments made directly or indirectly, in cash or in kind, related to the goods; |
| ለ/ ከዕቃው በቀጥታ እና ከዕቃው ጋር ከተያያዙ መብቶች ጋር በተገናኘ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ክፍያን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፣ | b) Detailed information or documents showing payments made or to be made directly related to the goods or associated rights; |
| ሐ/ ዕቃውን ለመግዛት የወጡ ሌሎች ወጪዎች የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ወይም ሰነድ፤ | c) Detailed information or documents showing other costs incurred to purchase the goods. |
| 4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃው እስከተጫነበት ወደብ ድረስ የተከፈለ ትራንስፖርትና ኢንሹራንስ ወጪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡- | 4) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the accuracy of transport and insurance costs paid up to the port of loading: |
| ሀ/ ዕቃው የተላከበት /Place of export/ ሀገርና ዕቃው በኮንቴነር የታሸገበት ቦታ ማስረጃ፣ | a) Evidence of the country of export and the location where the goods were packed in containers; |
| ለ/ ዕቃው በተላከበት ሀገር ወደብ እስኪደርስ የወጣ የማጓጓዣ ወጪ ማስረጃ | b) Evidence of transport costs incurred up to the port in the country of export; |
| ሐ/ በዕቃው ግብይት ወቅት ጥቅም ላይ የዋለ አለም አቀፍ የንግድ ውሎች /INCOTERMS/ | c) International commercial terms (INCOTERMS) used during the transaction. |
| 5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ከተጫነበት ወደብ እስከ መጀመሪያ የኢትዮጵያ መግቢያ በር ድረስ የተከፈለ የማጓጓዣና የኢንሹራንስ ወጪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡- | 5) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the accuracy of transport and insurance costs paid from the port of loading to the first entry gate of Ethiopia’s customs territory: |
| ሀ/ የማጓጓዣ እና የኢንሹራንስ ስምምነቱን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ፣ | a) A statement showing the terms of the transport and insurance agreement; |

ለ/ ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የወጣ የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪዎች ማስረጃ፣

b) Evidence of transport, loading, unloading, handling, and insurance costs incurred to deliver the goods to the first entry gate of Ethiopia's customs territory.

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የኮሚሽን ክፍያዎች ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

6) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of commission payments:

ሀ/ የውክልና ስምምነት ሰነድ፣

a) Agency agreement document;

ለ/ የኮሚሽን ክፍያ ዓይነት የሚገልጽ ሰነድ፣

b) Document specifying the type of commission payment;

ሐ/ የኮሚሽን ክፍያ ኢንቮይስ

c) Commission payment invoice.

7) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የማሸጊያ እና የመያዣ ወጪ ክፍያዎች ስለመኖራቸው እና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

7) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of packaging and container costs:

ሀ/ ዕቃውን ለማሸግ የወጣ የማቴሪያል ዓይነትና የጉልበት ወጪ፣

a) Type of materials and labor costs incurred for packaging the goods;

ለ/ ዕቃውን የማሸግ ስራው የተከናወነበት ቦታ ወይም ሀገር፣

b) Location or country where the packaging was performed;

ሐ/ ዕቃውን የማሸግ ሥራ ያከናወነው አካል፣

c) Entity that performed the packaging;

መ/ ከዕቃው ተነጥለው የማይታዩ የዕቃ መያዣ ወጪ፣

d) Costs of containers not separately identifiable from the goods.

8) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለላኪው ያቀረባቸውን ግብዓቶችና አገልግሎቶች ስለመኖራቸውና

8) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify

ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

the existence and accuracy of inputs and services provided to the exporter:

ሀ/ ዕቃውን ለማግኘት ወይም ለማምረት በገዢው በቀጥታ ወይም በገዢው ሥም በሶስተኛ ወገን በኩል ለአምራቹም ሆነ ለላኪው የቀረቡ ዕቃና አገልግሎቶች ዝርዝር፣

a) Details of goods and services provided by the buyer, directly or through a third party in the buyer's name, to the manufacturer or exporter for obtaining or producing the goods;

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) ፊደል ተራ (ሀ) ለተዘረዘረ ዕቃና አገልግሎት የማምረቻ ወጪ ወይም የግዢ ዋጋ እና የማድረሻ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣

b) Evidence showing the production or purchase costs and delivery costs for the goods and services listed in sub-article (8)(a) of this article.

9) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች ስለመኖራቸውና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

9) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of royalty and license fees:

ሀ/ በዕቃው ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን አካላት ሚናና ግንኙነት የሚያስረዳ መግለጫ፣

a) A statement explaining the roles and relationships of the parties involved in the transaction;

ለ/ የሮያሊቲና ፈቃድ ስምምነት ሰነድ፣

b) Royalty and license agreement document;

ሐ/ የሽያጭ ስምምነት ሰነድ፣

c) Sales agreement document;

መ/ ከዕቃው ግዥ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

d) Other documents related to the purchase of the goods.

10) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃን መልሶ ከመሸጥ ከሚገኘው ገቢ ላይ የሚከፈሉ ክፍያዎች ስለመኖራቸውና ትክክለኛነታቸው ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

10) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of payments made from the proceeds of reselling the goods:

ሀ/ የሽያጭ ስምምነት ሰነድ፣

a) Sales agreement document;

ለ/ ገዥው ዕቃውን መልሶ በመሸጥ፣ ለሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

b) Detailed evidence showing payments made directly or indirectly to the seller from the proceeds of reselling, transferring, or using the goods;

ሐ/ ከዕቃው ግዢ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሰነዶች፣

c) Other documents related to the purchase of the goods.

11) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተሰጠ ወይም የሚሰጥ የቴክኒክ ድጋፍ መኖሩና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

11) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of technical support provided or to be provided after the goods enter the country:

ሀ/ የዕቃ ወይም የአገልግሎቶች ግዢ ውል ሰነድ፣

a) Purchase contract document for the goods or services;

ለ/ ክፍያዎቹ ዕቃ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለወጡ ወጪዎች የተከፈሉ መሆናቸውን የሚያሳይ መግለጫ፣

b) A statement showing that the payments were made for costs incurred after the goods entered the country;

ሐ/ የተደረገው/የሚደረገው ድጋፍ ዓይነትና ወጪ መጠን ማስረጃ፣

c) Evidence of the type and cost of the support provided or to be provided;

መ/ ወጪዎቹ ለዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

d) Evidence showing whether the costs are included in the paid or payable value of the goods.

12) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የተከፈሉ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪዎች መኖራቸውንና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

12) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of transport and administrative costs paid after the goods enter the country:

ሀ/ ዕቃ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የወጣ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪ መኖሩን የሚያሳይ መግለጫ፣

a) A statement showing the existence of transport and administrative costs incurred after the goods entered the country;

| | |
|---|---|
| ለ/ የማጓጓዣ እና አስተዳደራዊ ወጪውን መጠን የሚያሳይ ማስረጃ፣ | b) Evidence showing the amount of transport and administrative costs; |
| ሐ/ የአገልግሎቱን ባህሪና ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ፣ | c) Evidence showing the nature and conditions of the service; |
| መ/ ወጪው ለዕቃው በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ መካተቱን ወይም አለመካተቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣ | d) Evidence showing whether the costs are included in the paid or payable value of the goods. |
| 13) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ተቀናሽ የፋይናንስ ወጪዎች መኖራቸውንና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡- | 13) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence and accuracy of deductible financial costs: |
| ሀ/ ወደ ሀገር ከገባው ዕቃ ግዥ ጋር በተያያዘ በገዢው የተከፈለውን የብድር ወይም የፋይናንስ ወለድ ክፍያና የክፍያ ስምምነት ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ፣ | a) Evidence showing the loan or financial interest payments made by the buyer in connection with the purchase of the imported goods and the terms of the payment agreement; |
| ለ/ ክፍያውን ዘግይቶ እንዲፈፀም የሚያስችሉ ስምምነቶች የሚያስረዳ ሰነድ፣ | b) Documents explaining agreements allowing delayed payment. |
| 14) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከሻጩ ጋር ግንኙነት ወይም ዝምድና ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶችና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡- | 14) Subject to the provisions of sub-article (1) of this article, the declarant must provide the following documents and evidence to verify the existence or absence of a relationship with the seller: |
| ሀ/ በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት ሁኔታና ዓይነት፣ | a) The nature and type of the relationship between the buyer and seller; |
| ለ/ በገዢና ሻጭ መካከል ያለው ግንኙነት በዕቃው ግብይት ዋጋ ጋር ያለው ተፅዕኖ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ፣ | b) Documentary evidence showing the impact of the relationship between the buyer and seller on the transaction value of the goods; |

ሐ/ የድርጅቱን ዝርዝር ፕሮፋይልና የዋጋ ፖሊሲ የሚያሳይ ሰነድ፣

c) Documents showing the company's detailed profile and pricing policy;

መ/ የገዢውና የማከፋፈል ወይም የኤጀንት /ብቸኛ ወኪል/ መብት ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፣

d) Documents showing the buyer's distribution or exclusive agency rights agreement;

ሠ/ የዕቃው የሽያጭ የውል ሰነድ እና የሻጩ ኢንቮይስ፣

e) Sales contract document and the seller's invoice;

ረ/ በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል የተከናወነ ሽያጭ /ወደ ኢትዮጵያ የተላከ/ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣

f) Detailed evidence showing the transaction value of identical or similar goods sold to Ethiopia at the same time between unrelated buyers and sellers;

ሰ/ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችና ሰነዶች

g) Other necessary information and documents.

**24. በአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ መሠረት ለመስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች**

**24. Information and Documents Required for Processing Based on the Value of Identical Goods**

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ዋጋውን መተመን ትክክል የሚሆንበትን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፣

1) A statement explaining why it is appropriate to value the goods based on this valuation method;

2) ከዕቃው በፊት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡ ነጠላ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ፣

2) Evidence showing the unit price at which identical goods were sold at the same commercial level and in comparable quantities before the goods entered the country;

3) በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ የገባ አንድ ዓይነት ዕቃ ማስረጃ፣

3) Evidence of identical goods imported into Ethiopia at the same or a comparable time;

4) የአንድ አይነት ዕቃ የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ /Price List/ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

4) Documentary evidence showing the manufacturer's sales price list for identical goods.

**25. በተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ መሠረት ለመስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች**

**25. Information and Documents Required for Processing Based on the Value of Similar Goods**

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣

1) A statement confirming the accuracy of the declared value of the goods based on this valuation method;

2) ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎች በተመሳሳይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት የተሸጡበትን ነጠላ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ፣

2) Evidence showing the unit price at which similar goods were sold at the same commercial level and in comparable quantities before the goods entered the country;

3) በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ጊዜ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃ ማስረጃ፣

3) Evidence of similar goods imported into Ethiopia at the same or a comparable time;

4) የተመሳሳይ ዕቃዎች የአምራች የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መረጃ /Price List/ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ፣

4) Documentary evidence showing the manufacturer's sales price list for similar goods.

**26. ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ዋጋን ለመተመን መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች**

**26. Information and Documents Required for Valuation Using the Deductive Method**

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣

1) A statement confirming the accuracy of the declared value of the goods based on this valuation method;

2) በሻጩ ወይም በዲክላራሲዮን አቅራቢው እና በገዢው ወይም በአከፋፋዩ ወይም በቸርቻሪው መካከል ያለውን የዝምድና ሁኔታ እና በዕቃው የሀገር ውስጥ መሸጫ ዋጋ ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ የሚያስረዳ ማስረጃ፣

2) Evidence explaining the relationship between the seller or declarant and the buyer, distributor, or retailer, and its impact on the domestic selling price of the goods;

3) የሽያጩን ሁኔታ የሚያስረዱ መረጃዎች ማስረጃዎች፣

3) Evidence and information explaining the conditions of the sale;

4) ሻጩ ወይም ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዕቃዎቹን የሚሸጥበት ዋጋ ዝርዝር ማስርጃ፣

4) Evidence of the price at which the seller or declarant sells the goods;

| | |
|---|---|
| 5) የሽያጭ ውል ሰነድ ወይም ኢንቮይስ እና ክፍያ የተፈጸመበት ማስረጃ፣ | 5) Sales contract document or invoice and evidence of payment |
| **27. የዕቃውን የጉምሩክ ዋጋ ወደ ኋላ በማስላት ዘዴ ለመስተናገድ የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች፣** | **27. Information and Evidence Required for Processing the Customs Value Using the Deductive Method** |
| 1) የዕቃው ወይም የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ መሸጫ ዋጋ እና የሽያጭ ወጪና ትርፍ ማስረጃ፣ | 4) Evidence of the selling price and sales costs and profit for the goods, identical goods, or similar goods; |
| 2) ከዕቃው ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ የወጡ ወጪዎችና ክፍያዎች ዝርዝር ማስረጃ፣ | 2) Detailed evidence of costs and payments incurred domestically in connection with the goods; |
| 3) ዕቃው ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ከመሸጡ በፊት የተከናወነ በምርት ሂደት የታከለ ተጨማሪ እሴት መጠን የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ፣ | 3) Detailed evidence of the value added through production processes before the goods are sold domestically after entering the country; |
| 4) ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የሚከፈል የቀረጥና ታክስ መጠን፣ | 4) The amount of duties and taxes paid for identical or similar goods imported into the country; |
| 5) የዕቃው የንግድ ዘርፍ አማካይ የኮሚሽን ወይም የትርፍ ምጣኔ ወይም የወጪዎችን ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣ | 5) Evidence showing the average commission or profit rate or cost rate for the commercial sector of the goods; |
| 6) የዕቃው የንግድ ዘርፍ አማካይ የማጓጓዝ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎችን ምጣኔ የሚያሳይ ማስረጃ፣ | 6) Evidence showing the average rate of transport, insurance, and other related costs for the commercial sector of the goods |
| **28. በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ የዋጋ ትመና ዘዴ መሠረት ለማስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች** | **28. Documents and information required for applying the cost-based customs valuation method** |
| 1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣ | 1) A statement confirming the accuracy of the declared value of the goods based on this valuation method; |

2) ዕቃዎቹ በላኪው የተመረቱና የተላኩ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ፣

2) Evidence showing that the goods were produced and exported by the exporter;

3) በላኪው ሀገር ዕቃዎቹን ለማምረት የወጣውን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪ የሚያሳይ ማስረጃ፣

3) Evidence of the production or preparation costs incurred in the exporter's country to produce the goods;

4) በላኪው ሀገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ ወይም የእቃው የንግድ ዘርፍ የመሸጫ፣ የማሸጊያና ሌሎች ወጪዎች እና የትርፍ መጠን ማስረጃ፣

4) Evidence of the sales, packaging, and other costs and profit margins when identical or similar goods are sold by manufacturers in the exporter's country or in the commercial sector of the goods;

5) ዕቃውን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማጓጓዝ፣ ለመጫን፣ ለማራገፍ፣ ለመንከባከብ፣ ለኢንሹራንስና ለሌሎች ተዛማጅ ስራዎች የተፈፀመ የክፍያ ማስረጃ፣

5) Evidence of payments made for transport, loading, unloading, handling, insurance, and other related activities to deliver the goods to the first entry gate of Ethiopia's customs territory.

## 29. ሚዛናዊ የዋጋ ትመና ዘዴ መሰረት በማድረግ ለመስተናገድ መቅረብ ያለባቸው መረጃዎችና ሰነዶች፣

## 29. Information and Documents Required for Processing Based on the Fallback Valuation Method

1) በዚህ የዋጋ አተማመን ዘዴ መሠረት ለመስተናገድ የቀረበው የዕቃ ዋጋ ትክክል መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ፣

1) A statement confirming the accuracy of the declared value of the goods based on this valuation method;

2) የዕቃውን ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ሰነዶች፣

2) Necessary information and documents to value the goods.

## 30. የዋጋ ውሳኔ ኢንስፔክሽን ስርዓት

## 30. Valuation Decision Inspection System

1) ዳይሬክቶሬቱ በየደረጃው የሚሰጡ የዋጋ ውሳኔዎች ህግና አሰራርን መሰረት በማድረግ የተወሰኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤

1) The Directorate shall establish a control system to ensure that valuation decisions made at each level are based on law and procedure.

2) የቅ/ጽ/ቤቶችን የዋጋ ውሳኔና የዋጋ አሰራሮችን ተአማኒነትና ህጋዊነት ለማረጋገጥ በየጊዜው የዋጋ ክለሳ ወይም እንደገና የማየት

2) Periodic reviews or revisions of valuation decisions and procedures of branch offices

ወይም የማረም ስራ ይሰራል፤ ስህተት ወይም ጥፋቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያቀርባል።

shall be conducted to ensure their reliability and legality; legal action shall be taken for errors or violations, and a report shall be submitted to the Commission.

## ክፍል ሶስት

## የዲክላራሲዮን አቅራቢ መብት እና ግዴታ

### 31. የዲክላራሲዮን አቅራቢው መብት

1/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በቅ/ጽ/ቤት በሚገኝ የስራ ክፍል በተሰጠ የዋጋ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ቅሬታውን ለዕቃ አወጣጥ የስራ ሂደት ያቀርባል።

2/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያልረካ እንደሆነ አቤቱታውን ለቅ/ጽ/ቤት የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ስራ ክፍል ያቀርባል፣

3/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያልረካ እንደሆነ አቤቱታውን ለኮሚሽኑ የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

4/ በኮሚሽኑ የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል።

## Part Three

## Rights and Obligations of the Declarant

### 31. Rights of the Declarant

1) If the declarant is dissatisfied with a valuation decision made by a working unit in a branch office, they may submit a complaint to the goods clearance work process.

2) If the declarant is dissatisfied with the decision made under sub-article (1) of this article, they may submit an appeal to the customs appeal review work unit of the branch office.

3) If the declarant is dissatisfied with the decision made under sub-article (2) of this article, they may submit an appeal to the Customs Appeal Review Directorate of the Commission.

4) Any person dissatisfied with the decision of the Commission’s Customs Appeal Review Directorate may file an appeal with the Federal Tax Appeal Commission within one month from the date of the decision.

5/ በፌደራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው በየደረጃው ላለው ፍርድ ይግባኙን ማቅረብ ይችላል።

5) A person dissatisfied with the decision of the Federal Tax Appeal Commission may file an appeal at the relevant judicial level.

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በኮሚሽኑ የዋጋ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው በኮሚሽኑ በተወሰነው የዋጋ ውሳኔ መሠረት የዕቃውን ቀረጥና ታክስ መጠን ዋስትና በማስያዝ የኮሚሽኑን የመጨረሻ ውሳኔ ሳይጠብቅ የዕቃ መልቀቂያ ማግኘት ይችላል።

6) Subject to sub-article (2) of this article, a person with a complaint regarding the Commission's valuation decision may secure the release of the goods without awaiting the Commission's final decision by providing a guarantee for the customs duty and tax amount based on the Commission's valuation decision.

## 32. የዲክላራሲዮን አቅራቢ ግዴታ

## 32. Obligations of the Declarant

1) በጉምሩክ አዋጅና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን እና የጉምሩክ ዝርዝር የዋጋ መረጃ እንዲሁም ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ አባሪ ሰነዶች ጋር የማቅረብ፤

1) Submit the customs declaration, customs valuation detail information, and supporting documents necessary for customs procedures in accordance with the Customs Proclamation and this directive.

2) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ኮሚሽኑ በሚወስነው ዘዴ በሚዘጋጁ ቅጾች ወይም ሰነዶች ላይ መረጃዎችን በአግባቡ በመሙላት እና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ የማቅረብ፤

2) The declarant must properly complete the information on forms or documents determined by the Commission and verify their accuracy before submission.

3) ዲክላራሲዮን አቅራቢው ሞልቶ እና አረጋግጦ ባቀረበው መረጃና ሰነድ ላይ ለሚገኝ ማንኛውም ስህተት ሙሉ ኃላፊነት አለበት።

3) The declarant bears full responsibility for any errors in the information and documents provided and verified.

# ክፍል አራት

# Part Four

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Miscellaneous Provisions

## 33. የገንዘብ ምንዛሪ

## 33. Currency

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ ዲክላራሲዮኑ ለጉምሩክ ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት እለት በኢትዮጵያ

The customs duty and tax assessment value shall be based on the foreign currency exchange rate determined by the National

ብሔራዊ ባንክ በሚወሰነው ተመን መሰረት ይሆናል፡

Bank of Ethiopia on the date the declaration is submitted and accepted for customs purposes.

## 34. የተደራጀ የጉምሩክ የማነፃፀሪያ ዋጋ መረጃ አጠቃቀም

## 34. Use of Organized Customs Reference Price Information

1) ዳይሬክቶሬቱ ወደ ሀገር የሚገቡ እቃዎችን ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራትና ሥጋት ለመወሰን እንዲያስችል በጉምሩክ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የጉምሩክ ዋጋ ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ የመረጃውን ጥራት ይከታተላል።

1) The Directorate shall organize, update, and monitor the quality of customs valuation data to verify the accuracy of the value of imported goods and assess risks, as authorized by the Customs Proclamation.

2) ለማነፃፀሪያነት የሚውሉ መረጃዎች በዋናነት ለንግድ አላማ በብዛት የገቡ ዕቃዎች ዋጋ ሲሆን የንግድ ዕቃዎች ዋጋ በመረጃ ሥርዓት በማይገኝበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ተጣርተው ወደ መረጃ ሥርዓት የገቡ የአምራች ድርጅቶች ዋጋ በማነጻጸሪያነት ሊያገለግል ይችላል።

2) The data used for comparison primarily consists of the prices of goods imported in large quantities for commercial purposes. When the price of commercial goods is not available in the data system, the prices of goods from manufacturers entered into the system after verification may be used for comparison as necessary.

3) በጉምሩክ የማነፃፀሪያ ዋጋ መረጃ ውስጥ የገቡ መረጃዎችን ከዚህ በታች በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት የእቃዎች ዋጋ ውሳኔ ይሰጣል፡-

ሀ/ አውቶማቲክ ሞጁል /ECVS-Automatic Analysis/

ለ/ ኩዌሪ ቢዩልደር ሞጁል /ECVS-Automatic Query Builder Moudule/

ሐ/ አለምአቀፍ ዋጋ ሞጁል /ECVS-International Price/ IP/

3) Decisions on the valuation of goods shall be made based on the data in the customs reference price system in the following order of priority:

a) Automatic Module (ECVS-Automatic Analysis)

b) Query Builder Module (ECVS-Automatic Query Builder Module)

c) International Price Module (ECVS-International Price/IP)

## 35. የጉምሩክ መረጃ ሚስጥራዊነት

## 35. Confidentiality of Customs Information

ዲክላራሲዮን አቅራቢው ከሚያቀርበው መረጃ በመነሳት ኮሚሽኑ የዋጋ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ጊዜ በዲክላራሲዮን አቅራቢ የሚቀርበውን መረጃ በማጣራት እና የተሟላ በማድረግ ሂደት የሌሎችን ዲክላራሲዮን አቅራቢዎች መረጃ ሚስጥራዊነት መጠበቅ አለበት።

When making a valuation decision based on the information provided by the declarant, the Commission must verify and complete the information while ensuring the confidentiality of other declarants' information.

## 36. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

## 36. Repealed and Inapplicable Laws

የገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 158/2011 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

The Customs Duty and Tax Assessment Value Directive No. 158/2011 is repealed by this directive.

## 37. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

## 37. Transitional Provisions

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ በሂደት ላይ የነበሩ ጉዳዮች በነባሩ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ።

Cases initiated and in progress (pending cases) before the issuance of this directive shall be decided based on the existing directive.

## 38. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

## 38. Effective Date of the Directive

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገቢዎች ሚኒስቴር ድረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

This directive shall take effect as of the date of its registration with the ministry of justice and its uploading on the ministry of revenues.

**ዓይናለም ንጉሴ አሊ**

**የገቢዎች ሚንስቴር ሚኒስትር**

**2017**

**Aynalem Nigussie Ali**

**Minister Ministry of Revenues**

**2025**